ቀን 19/02/2009 ዓ.ም

**ጉዳዩ: - ስለ በገ/ኢ/ት/ሚ የሚሰሩ የመንግስት ሰራተኞች እና የድርጅት አባላት ላይ እየደረሰ ያለው የማስፈራራት እና ከስራ የማገድ ተግባሮች ማጋለጥ ይሆናል**

ይህ ፅሁፍ ስለ በገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚንስትር ላይ የሚሰሩ የመንግስት ሰራተኞች እና የድርጅት አባላት ላይ በክቡር ሚንስትር ዴኤታው አቶ አለማየ ጉጀ በኩል እየደረሱት ያሉትን የማስፈራራት እና የማሸማቀቅ ተግባሮች ይገልፃል : : ምንም እንኳን የተለያዩ በደሎች በአብዛኞው የድርጅት አባላት ላይ እየተፈፀመ ቢሆንም ለግዜው ግን በዚህ ፅሁፍ ላይ ስለ በግንባር ቀደምነት የሚጠቀሱ ሁለት ሰራተኞች እና የድርጅት አባላት ላይ አትኩረን ፅፈናል : : እነሱም : -

1) **አቶ ብርሃኑ ፀጋይ :** በ ገ/ኢ/ት/ሚ ውስጥ የሚገኘው IFMIS (ኢፍሚስ) በሚባለው Project ላይ የሚሰሩ ሲሆኑ : እንዲሁም በመ/ቤቱ ውስጥ ያለው የህወሃት ህዋስ ሰብሳቢ እና የኢህአዴግ መሰረታዊ ድርጅት የፖለቲካ ዘርፍ ሰብሳቢ ናቸው : :
2) **አቶ አብራሃም ሙሉጌታ :** በ ገ/ኢ/ት/ሚ ውስጥ የሚገኘው IFMIS (ኢፍሚስ) በሚባለው Project ላይ የሚሰሩ ሲሆኑ : እንዲሁም በመ/ቤቱ ውስጥ ያለው የደኢህዴን ህዋስ ሰብሳቢ እና የኢህአዴግ መሰረታዊ ድርጅት የአደረጃጀት ዘርፍ ሰብሳቢ ናቸው : :

እነዚህ ሁለት ሰራተኞች በየመንግስት እና በየድርጅት ስራቸውና አመራራቸው የተመሰገኑ መሆናቸውን በማንኛውም መንገድ ማረጋገጥ ይቻላል : : በ ገ/ኢ/ት/ሚ ላይ ስር ሰዶ ያለውን የኪራይ ሰብሳቢነት እና የመልካም አስተዳደር እጦት እነዚህ ሰዎች በተደረጉት የተለያዩት የመ/ቤታቸው ስብሰባዎች ላይ በግንባር ቀደምነት በግልፅና በአደባባይ ሲታገሉ የመጡ በዚህም መላው የመ/ቤታቸው ሰራተኞች የሚያውቋቸው ታጋዮች ናቸው : :

ሆኖም ግን በዚህ ምክንያት በአንዳንድ የመ/ቤቱ ከፍተኛ ባለ ስልጣኖች በጥሩ ዓይን አልታዩም : : በተለያዩ ግዜ ደሞ በግላቸው ላይ የተለያዩ የማስፈራራት እና የማሸማቀቅ ተግባሮች ደርሶባቸዋል : : ለምሳሌ ከደረሱባቸ የተለያዩ ማስፈራርያዎች ጥቂቶቹ ለመግለፅ ያህል : -

ከአንድ ዓመት በፊት ኣቶ ብርሃኑ ፀጋይን በተቀነባበረ ሴራ የዲሲፒሊን ጉዳይ (ሴክረታሪን "ተሳድበሃል") በማለት የውሸት ክስ የመ/ቤቱን የዲሲፒሊን ህግ ጉዳይ የአፈታት መንገድ ሳይከተል ሴክረታሪዋን ሆንብላ እንድትከሰው በማድረግ የክስ ወረቀት ቀጥታ ከሴክረታሪዋ ቀጥታ ወደ ክቡር ሚንስትር ዴኤታው ኣቶ ኣለማየ ጉጀ እንዲደርስ ተደረገ : :

- ወድያውኑ ሚንስትር ዴኤታው በስርዓቱ መሰረት የክሱ ሃቅነት ሳያጣሩ አቶ ብርሃኑ ፀጋይን ወደ ቢሮአቸው ጠርተው እንዲህ ብለው የማስፈራርያ ቃላቶች ተናገሩት ፡- **“ እኔ ብፈልግ በዝቺ የክስ ወረቀት ብቻ ከስራህ ላባርርህ እችላሎ ፡፡“** ሱሉት ፡
- አቶ ብርሃኑ ደሞ **“እኔ ባላጠፋሁት ጥፋት ወይም ደሞ በዲስፒሊን ኮሚቴ ታይቶ ተረጋግጦ *‘ጥፋተኛ ነህ’* እስካልተባልኩ ድረስ ከስራየ ልባረር አልችልም ፡፡”** ብሎ ይመልስላቸዋል፡፡
- ቀጥለው ሚንስትር ዴኤታው እንዲህ ይሉታል **“ አንዳንድ የፖለቲካ ይሁን ሌሎች ፅሁፎችና ደሞ ኮፒ እያደረክ የመ/ቤታችን ገበና እያወጣህ ለሌሎች ባለ ስልጣናት ትሰጣለህ ፡፡”** ሲሉት ፡
- አቶ ብርሃኑ ደሞ **“ ክቡር ሚንስትር አሁንም ይህ ያሉት ነገር እውነት አይደለም ሆኖም ግን እኔ እንደ የመ/ቤታችን የህወሓት ህዋስ ሰብሳቢ አንዳንድ የድርጅት ሪፖርት ሲኖሩ ግን እውነት ነው በየመንግስት ንብረት ፎቶ ኮፒ አደርጋሎ ይሄ ደሞ የኔ ችግር ሳይሆን የሁላችን ችግር ነው ታድያ የድርጅት ሪፖርት የት ሂጀ ፎቶ ኮፒ ላድርግ ፡፡”** ብሎ ይመልስላቸዋል ፡፡
- በስተመጨረሻ ሚንስትር ዴኤታው እንዲህ ይሉታል **“ አንተ የ Project ቱ ማናጀር መሆን ከፈለክ ማናጀር ላደርግህ እችላሎ ፡ ብቻ አንተ እነዛ አንዳንድ ኮፒ እያረክ ለሌሎች ባለ ስልጣናት የምትሰጠው ነገር አቁም ፡፡”** ሲሉት ፡
- አቶ ብርሃኑ ደሞ **“ ከዚህ በፊት እርሶ በስብሰባ ላይ እንደተናገሩት (*<u>‘የፕሮጀክቱ ማናጀር ለመሆን አቅም አለን የምትሉ ሰራተኞች ካላቹ ማመልከት ትችላላቹ ’</u>*) ባሉት መሰረት እኔ እንደ ማንኛው ሰራተኛ ማመልከቻየን አስገብቻሎ ፡ በዚህ መሰረት የትምህርት ደረጃዮ እና የስራ ልምዴን ማለትም Merit-based በሆነ መልኩ ካሸነፍኩኝ ማናጀር መሆን እችላሎ ፡፡”** ብሎ ከመለሰላቸው በሃላ ተለያዩ ፡፡

በሗላ ግን በሚንስትር ዴኤታው ተደጋጋሚ የማስፈራራት ቃላቶች ለመረዳት ይተቻለው ነገር ቢኖር አቶ ብርሃኑ <u>የዲስፒሊን ችግር ስለነበረበት ሳይሆን በገ/ኢ/ት/ሚ ስር የሰደደውን የኪራይ ሰብሳቢነት ችግሮች እየፃፍክ እና ኮፒ እያደረክ ለሌሎች ባለ-ስልጣናት አሳልፈህ እየሰጠህ ነው</u> ፡፡ የሚል ማረጋገጫ የሌለው አቋም እንደያዙ ነው የሚያሳየን ፡፡

## <u>እስካሁን ድረስ ከላይ የተገለፁት ተግባሮች ከአንድ ዓመት በፊት የተፈፀሙ ናቸው፡፡</u>

## ቀጥለው የተገለፁት ተግባሮች ደሞ ባለፍት ሁለት ወራት የተፈፀሙ ናቸው፡ :

በመቶ ሚሊዮን ዶላሮች የሚሰራው በገ/ኢ/ት/ሚ ውስጥ የሚገኘው IFMIS (ኢፍሚስ) የሚባለው Project ከሁለት ወር በፊት የተዘጋጀለት አዲስ የ Project office structure ወይም መዋቅር መሰረት በማድረግ : ፕሮጀክቱ አንድ ማናጀር ሲኖሮው፡ ከስር ደሞ ሶስት ምክትል ማናጀሮች : ቀጥሎ ደሞ ዘጠኝ የቡድን መሪዎች : እና ቀጥሎ ደሞ አንድ መቶ የሚሆኑ ሲኔር እና ጀኔር ኤክስፐርቶች አሉት : : በአጠቃላይ 110 ሰራተኞች የያዘ Project ነው : :

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የፕሮጀክቱ የቦታ ክፍፍል (ወይም ለሰራተኛው position አሰጣጥ) ፈፅሞ merit-based ያልሆነ እና እንዲሁም የስቪል ሰርቫንቱን ሕግ የጣሰ እንዲሁም የመንግስት ሰራተኛው መብት የረገጠ ነው : : ይህንን ለማረጋገጥ በቀላሉ የፕሮጀክቱን ሰራተኞቹን መጠየቅ ወይም ደሞ የሰራተኛውን File በማየት ማን የትኛው position ላይ እንዳለ ሲታይ ከጠቅላላ 110 ሰራተኛ ከ 90 ከመቶው ህገ-ወጥ በሆነ አሰራት ነው የተመደበው ቢባል ማጋነን አይሆንም : :

ይህ የሰራተኛውን መብት የጣሰ አሰራር ያስተዋሉ ሁለት የኢህአደግ ኣባላት ወደ ክቡር ሚንስትር ዴኤታ ኣቶ ኣለማየ ጉጆ ቢሮ በመሄድ የፕሮጀክቱ ሰራተኛ አመዳደብ ስርዓት merit መሰረት ያላደረገ እና ትክክል አለመሆኑ ቅሬታቸው ለሚንስትር ዴኤታው ሲያቀርቡ : የሚንስትር ዴኤታው መልስ ግን የሚገርም መልስ ነበር ያጋጠማቸው እንዲህም የሚል ነበር “ **የሰራተኛው አመዳደብ merit-based ይሁን አይሁን እናንተ መጠየቅ አትችሉም አያገባቹሁም** ” በማለት ከአንድ ከፍተኛ የመንግስት ባለ ስልጣን ለዛውም ሚንስትር ዴኤታ የሆነ ሰብ ፈፅሞ የማይጠበቅ መልስ ነበር የተሰማው : : የሚንስትር ዴኤታው መልስ ያላረካቸው ቅሬታ አቅራቢ ሰራተኞች ለሚንስትር ዴኤታው እንዲህ ብለው ይመልሱለታል : -

> “ **እኛ እንደ የ Project ቱ ሰራተኞች የመጠየቅ መብት እኮ አለን የሰራተኛው አመዳደብ ልክ አይደለም : : የመንግስት ወይም የ ሲቪል ሰርቫንቱን ሕግ የተከተለ አይደለም : : በዚህ ላይ እኛ እንደ የድርጅት አባላት ከማንም በላይ የመንግስት ስርዓት ያልተከተለ አሰራር ካለ የመጠየቅ እና የመታገል ግዴታ አለብን** : :“ አሉት

ሚንስትር ዴኤታው ደሞ ተበሳጭቶ እንዲህ ይላቸዋል “ **የድርጅት አባላትም ብትሆኑ መጠየቅ አትችሉም ይህ የማናጅመንቱ ውሳኔ ነው : : ደሞ አንተ (ኣቶ ኣብርሃም ሙሉጌታ) እኮ የደርግ ወታደር ነበርክ : እዚህ Project ውስጥ እንድትገባ ያደረኩህ እኮ እኔ ነኝ : ይሄ የምትተማመንበት ደጓኛህ (ኣቶ ብርሃኑ ፀጋይ) ፊት ላይ ነው የምነግርህ : : የምታመጣው ነገር የለም** : : ” ብሎ ሲናገራቸው ሰራተኞቹ “ **እሺ** ” ብለው ከየሚንስትር ዴኤታው ቢሮ ወጥተው ሄዱ : :

ከዚህ በፊትም ሚንስትር ዴኤታው አቶ ኣብርሃም ሙሉጌታን **" አንተ እኮ የትግሬዎች አሽከር ነህ ! "** ብለው እንዳሉት ራሱ ኣቶ ኣብርሃም ነግሮናል : :

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከተወሰኑ ቀናት ቦሃላ ወደ የገ/ኢ/ት/ሚ ውስጣዊ E-mail ላኪው ማን እንደሆነ የማይታወቅ በውስጣዊ E-mail የተለያዩ የአሰራር ቅሬታዎችን የሚገልፅ ሁለት ገፅ ያለው ፅሑፍ ወደ መላው 110 የፕሮጀክቱ ሰራተኞች ውስጣዊ E-mail ይበተናል ወይም ይላካል : :

ቦሃላ ስለዚህ በ E-mail የተላከው ፅሁፍ ጉዳይ ክቡር ሚንስትር ዴኤታው ይደርሳቸውና ሚንስትር ዴኤታው ከዚህ በፊት በአካል ቀርበው ቅሬታቸው በህጋዊ መልኩ ላቀረቡ ሁለት የፕሮጀክቱ ሰራተኞችን ወደ ቢሮቸው ጠርተው እንዲህ ብለው ያስፈራሯቸዋል **" ይህንን በ E-mail ተፅፎ የተበተነው ፅሁፍ እናንተ ናቹ የፃፋቹሁት እሙኑ ካልሆነ ከዚህ Project ነው የማባርራቹ** : : " ሲሏቸው :

ሁለቱም ሰራተኞችም ደሞ እንዲህ ብለው ይመልሳሉ **" እኛ ይህንን ፅሁፍ ኣልፃፍንም እኛ ራሳችን እርሶ ጋር በአካል ቀርበን ቅሬታችን በግልፅ አቅርበን እያለን : እኛ እርሶ ጋር በአካል ቀርበን የጠየቅነው ጥያቄ በድብቅ ለዛውም በ E-mail ምንአፃፈን** : : " ሲሉዋቸው :

**"ደህና ሂዱ እንተያያለን** : :" ብለው ሚንስትር ዴኤታው ተናገሩ : :

ቦሃላ ከተወሰኑት ቀናት ቦሃላ ለነዚህ ከዚህ በፊት ቅሬታቸው በአካል ቀርበው በግልፅ የተናገሩት ሁለት የፕሮጀክቱ ሰራተኞች በቀን 02/02/2009 ዓ.ም በሚንስትር ዴኤታው የተፈረመ እንዲህ የሚል ደብዳቤ ደረሳቸው " **ከጥቅምት 02 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ የዓመት ዕረፍት እንዲወጡ የተወሰነ መሆኑን እንገልፃለን** : : " የሚል : *(ደብዳቤዎቹ ከዚህ ፅሁፍ ጋር ተያይዞ ቀርበዋል)*

እንደገና በነገታው አጠቃላይ የፕሮጀክቱ ሰራተኞችን የጠራ ጠቅላላ ስብሰባ በየፕሮጀክቱ ማናጀር በኩል ስብሰባው ይጠራል በዚህ መሰረት እነዚህ ሁለት የግዴታ ዕረፍቲ የሚገልፅ ደብዳቤ የተፃፈባቸው ሰራተኞች ከየፕሮጀክቱ ስብሰባ አደራሽ በሃይል ወይም በግድ እንዲባረሩ ተደረገ : :

በመቀጠል ስብሰባው ካለቀ ቦሃላ ካሉት 110 ጠቅላላ የፕሮጀክቱ ሰራተኞች እነዛን ሁለት ሰራተኞችን ወደ ጎን በመተው ለተቀሩት 108 ሰራተኞች የዓመታዊ contract ደብዳቤያቸው በማደስ እንዲሁም የደሞዝ ማሻሻያ በማድረግ ለያንዳንድ 108 ሰራተኛ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው ተደረገ : : እነዛ ሁለት ሰራተኞች ግን በአካል ቀርበው የመብት እና የግልፅነት ጥያቄ በህጉ መሰረት ስለጠየቁ ከህጋዊ መብታቸው ተጠቃሚ እንዳይደረጉ ተደረገ : :

በመቀጠል እንደገና ከተወሰኑት ቀናት ቦሃላ ለነዚህ ሁለት ሰራተኞች በቀን 09/02/2009 ዓ.ም አሁንም በክቡር ሚንስትር ዴኤታው የተፈረመ እንዲህ የሚል ደብዳቤ ለሁለተኛ ግዜ ደረሳቸው : -

**" ከጥቅምት 02 ቀን 2009 ዓ.ም በቁጥር ገ/ኢ/1/84/561 በተፃፈ ደብዳቤ እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ የዓመት ዕረፍት እንዲወጡ መወሰኑን ያሳወቅንዎት መሆኑ ይታወሳል : : ስለዚህ አንዳንድ የተፈፀሙ የዲስፒሊን ግድፈቶች አሉ የሚሉ ጉዳዮች ስላሉ እነዚህኑ የማጣራት ሂደት እንዲሳካ ለመረጃዎቹ አሰባሰብ ሲባል የእርስዎ ከመ/ቤቱ ውጪ መቆየት ተገቢ ሆኖ ስለተገኘ የዕረፍት ጊዜው ተጠናቆ ተለዋጭ መመሪያ እስከሚሰጥ ድረስ በመ/ቤቱም ውስጥ ሆነ ቅጥር ግቢ ከመገኘት እንዲታቀቡ እናሳስባለን : : "** ይላል : : *(ደብዳቤዎቹ ከዚህ ፅሁፍ ጋር ተያይዞ ቀርበዋል)*

እንደገና በመቀጠል ከተወሱት ቀናት በሃላ ለ 3ተኛ ግዜ በቀን 15/02/2009 ዓ.ም የተፃፈ ሆኖም ግን በሁለቱ ሰራተኞች እጅ ላይ ያልደረሰ ***(በ 2ኛው ደብዳቤ ምክንያት ወደ መ/ቤታቸው ቅጥር ግቢ እንዳይ ገቡ ስለተከለከሉ)*** አሁንም በክቡር ሚንስትር ዴኤታው የተፈረመ ጠቅለል ባለመልኩ የደብዳቤው ይዘት እንዲህ እንደሚል ሰምተናል : - *በአሁኑ ወቅት በገ/ኢ/ት/ሚ ውስጥ ከሚገኘው IFMIS (ኢፍሚስ) Project ላይ ብ **19,000** ብር ወርሃዊ ደሞዝ ሚሰሩበት ከነበረው Project ታግደው ወይም ደሞ ተባርረው ከሶስት ዓመት በፊት በ **4,000** ብር ወርሓዊ ደሞዝ ወደ ይሰሩበት የነበረው የቀድሞ የስራ ክፍላቸው እንደተመለሱ የሚገልፅ ደብዳቤ ነው : :*

ስለዚህ ባጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት በክቡር ሚንስትር ዴኤታ ኣቶ ኣለማየ ጉጆ ፊርማ ለሁለቱም ሰራተኞች በአንድ ወር ውስጥ የተፃፉት ሰወስት ተከታታይ ደብዳቤዎች መሰረት የሌላቸው እና ምክንያታቸው በግልፅ ያልታወቀ ደብዳቤዎች ለእነዚህ ሁለት ሰራተኞች ወደ ሚኒስትር ዴኤታው በኣካል ቀርበው የሙብት ጥያቄ በግልፅ ስለጠየቁ በአሁኑ ወቅት ከየመንግስት እና ከይድርጅት ስራዎቻቸው ተፈናቅለው ይገኛሉ : : ከዚህም በላይ እነዚህ ተከታታይ ደብዳቤዎች በአሁኑ ወቅት መንግስታችን ያወጀው **የኣስቸኳይ ግዜ ኣዋጅ አንቀፅ 4** ን በግልፅ የጣሱ ናቸው : :

በ ገ/ኢ/ት/ሚ መ/ቤት ያለው ብዙ የኪራይ ሰብሳቢነት እና የመልካም አስተዳደር እጦትን በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ በመገኘት በድፍረት እና በግልፅ እየታገሉ የመጡ ግንባር-ቀደም የመ/ቤታችን ሰራተኞች እና የድርጅቶቻችን ኣባላት ናቸው :: ስለሆነም ደሞ የሚመለከተው የመንግስት አካል በተለይ ደሞ የሚመለከተው የድርጅት አካላት ለእነዚህ ሁለት ሰራተኞች አፋጣኝ መፍትሄ እንዲሰጣቸው እንጠይቃለን ::

**እናመሰግናለን !**